በማህበረሰብ ዉይይት የተነሱ ዋና ፍሬ ነገሮች

# የዘር ፍትሃዊነት እና ማህበራዊ ፍትሃዊነት ወርክሾፕ

“ ኮቪድ-19 ሰዎች ሊለውጡ እንደሚችሉ አሳይቷል። በእግራቸው የሚሄዱ እና ብስክሌት የሚነዱ ሰዎች አሉ…አሁን ይሄንን በመደበኛ ሁኔታ ሲያደርጉ ደህንነት የሚሰማቸው ከሆነ ያስቡ….”

“ ተከራዮች አብዛኛውን ጊዜ ኋይል የሌላቸው መስሎ ይሰማቸዋል እና ከአከራዮቻቸው ምንም ድጋፍ ሳያገኙ በቤታቸው ውስጥ ከሚመጣው ጎርፍ የሚመነጩ እውነተኛ የሕይወት ጠንቆችን እንዲቋቋሙ ይደረጋሉ።

“ ብዙ ሰዎች በኮቪድ-19 የተነሳ ስራ የላቸውም ወይም ገቢያቸው አነስተኛ ነው፣ እና በጤና እና በጎነት፣ እና በወጪ መካከል እየጨመረ የመጣ አንዱን ከአንዱ የመምረጥ ሁኔታ አለ። “

> **የሞት የሽረት ሁኔታ ውስጥ እና ቀን በቀን እንደምንም ብለው ለማለፍ የሚጥሩ ሲሆኑ የአየርንብረትን ቅድሚያ መስጠት በጣም አዳጋች ነው።**

“ ሰዎች ትተው ያለፉትን የስሜት ቁስል ሁኔታዎችን ያስታውሳሉ፣ እና የጥቁራን ማህበረሰብ በስርዓት የሚደገፍ የዘር መድሎ ተጋላጭ መሆናቸው ቀጥለዋል። የስሜት ቁስል እና የአዕምሮ ጤና ላይ ቁልፍ ነገሮች ናቸው።”

“ ብዙ ስደተኛ ቤተሰቦች ከሕክምናው ስርዓት ጋር በተያያዘ የተወሰነ ፍርሃት ወይም ስጋት አለባቸው… እና እንዴት ይሄንን ነገር እንደሚወጡት ላያውቁ ይችላሉ።”

## በማህበረሰብ ዉይይት የተነሱ ዋና ፍሬ ነገሮች

# የመካች አምባሳደር የዳሰሳ ጥናት

“ስለ የጸሐይ ማመንጫ ኋይል የበለጠ እንደ ደንበኛ ለማወቅ እፈልጋለሁኝ፣ ምክንያቱም ብዙ ከመጠን በላይ መረጃ የቀረበልኝ ይመስለኛል። የጸሐይ ማመንጫ ኋይል ጥቅሙ ምንድን ነው፣ እና ከእኔ ከአሁኑ የመብራት ኋይል አጠቃቀም እንዴት ሊወዳደር ይችላል? በእኔ የክፍያ ደረሰኝ ላይ የሚከፈሉት ተጨማሪ ክፍያዎች ወደ ንጹህ የኋይል ማመንጫ ድጎማ ይሄዳሉ? የሚቀርቡት አማራጮች ሕጋዊ ይሁኑ ወይም አይሁኑ ማወቅ ይከብዳል። ከኋይል ማመንጫው የኋይል ማመንጫ አማራጮች ውጪ ከከባቢ አንፃር ተገቢ ስለሆኑት ጠቃሚ የደንበኛ መረጃዎች ማግኘት እፈልጋለሁኝ።”

“የኔ ጉዞ አስራአምስት-ደቂቃ የመኪና መንገድ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በአውቶብስ 45 ደቂቃዎችን ወይም በባቡር 1 ሰዓት ሊወስድብኝ ይችላል ምክንያቱም መኪና ስለሌለኝ ነው።”

“የተሻሉ፣ የበለጠ ቀጥተኛ የሕዝብ መጓጓዣ ማግኘት፣ ልክ ከአውቶብስ ማቆሚያ ወደ ሜትሮ መገናኛዎች የመሳሰሉት [በመኪና] የመጓጓዝ ፍላጎቴን ሊቀንሱ ይችላሉ። ”

“ብክለትን ለመቀነስ እና የማህበረሰቡን ጤና ለማሻሻል ንጽህ የኋይል ማመንጫ መምረጥ አለብን።”

ሞንትጎመሪ ካውንቲ

“የእግረኛ መጓጓዣ መንገድ ጥገና አለመኖር በእግር ለመጓዝ እና ብስክሌት ለመንዳት በጣም አዳጋች ያደርገዋል። ይሄ መኪና ለመግዛት አቅም ለሌላቸው ሰዎች አሉታዊ ተጽእኖዎችን ያሳድራል።”

“እኔ እንደማስበው ሳይንስ የአየርንብረት ለውጥ ታላቁ መንስኤዎች ውስጥ አንዱ በጎዳና ላይ ያሉት ሁሉም መኪናዎች እንደሆኑ እንዳሳየን አላውቅም። እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ፣ በመኪና የሚጓዙ ብዙ ሰዎች አሉን።”

“ከእነዚህ መኪናዎች ውስጥ አንዳንዶቹን ከጎዳና እንዲወጡ ለማድረግ ለመሞከር ማንኛውም ነገር ያደርጋል። ኳረንታይን ሲጀመር ጊዜ በጣም ምርጥ ነበር። አየሩ በጣም ንጽህ እና ትኩስ ነበር ምክንያቱም ሰዎች መኪና እየነዱ አልነበረም።”

# በማህበረሰብ ዉይይት የተነሱ ዋና ፍሬ ነገሮች

## የመካች አምባሳደር የዳሰሳ ጥናት

*“ከኤሌትሪክ አውቶብሶች እና መኪናዎች ጋር ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁኝ። አብዛኛዎቹ የማህበረሰብ ማዕከላት ላይ፣ የኤሌትሪክ ባትሪ መሙያ ጣቢያዎች እንዳሉ በማየቴ በጣም ደስተኛ ሆኛለሁኝ።”*

*“ድርጅቶች የሰራተኛ ኋይሎቻቸውን በኢንቴርኔት የመስራት ነፃነት እንዲኖራቸው ቁርጠኝነት እንዲያሳዩ መጠየቅ አለብን።
ይሄ በመንገድ ላይ አነስተኛ መኪናዎች እንዲኖሩ እና ሰዎች የቅልጥፍና እና የስራ ሕይወት ሚዛን እንዲኖራቸው ያስችላል።”*

**ወንድሜ በአስም ይሰቃያል እና ከቤት በመውጣት በእግር ጉዞ ማድረግ ብቻ ለመተንፈስ አዳጋች ይሆናል። የበለጠ የኋይል ወጪ ቆጣቢነት እና ንጽህ አየር እፈልጋለሁኝ።”**

**እኔ እንደማስ በው ኤልትሪክ መኪናዎች በካውንቲው ውስጥ ያለውን ብክለት ለመቀነስ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ዋጋቸው የሚያዋጣ መሆን አለባቸው።”**

*በማህበረሰቤ ውስጥ ያሉት አረንጓዴ ቦታዎች በተፈጥሮ የተከበብኩኝ ያህል እንዲሰማኝ ያግዙኛል። ንጹህ አየር እንድተነፍስ እና የከተማውን ከባቢ እንድርቀው ያግዙኛል። እነዚህ ቦታዎች ጥቂት ሰዎች ብቻ ገንዘብ በመክፈል ሊኖርቧቸው ከሚችሉት ለወደፊቱ ከሚደረጉ ልማቶች ጥበቃ ይደረግላቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁኝ።”*

*የመጠለያ ዛፎች እና ዛፎች በአጠቃላይ ቦታውን ቅዝቃዜ እንዲኖር ማድረግ አለባቸው።”*

*በቤቶች እና አፓርታማዎች ላይ የተሻለ የዛፍ ሽፋን መኖር የአውቶብስ ማቆሚያ ላይ የተሻለ መጠላያን ጨምሮ እያደገ የሚመጣ መጠለያ፣ ብዙ አውቶብስ አጠቃቀሞችን ያበረታታል እና ትራፊክን ይቀንሳል።”*

## በማህበረሰብ ዉይይት የተነሱ ዋና ፍሬ ነገሮች

### የመካች አምባሳደር የዳሰሳ ጥናት

*“አምቅ በሆነው አየርንብረት ላይ መተፈንስ በጣም ከባድ ነው። ሰዎች ራሳቸውን ሊስቱ እና ከፍተኛ ብር የሚከፍሉበት ሆስፒታል ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።”*

*“እያንዳንዱ ሰው በቤታችን ውስጥ በቂ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ያስፈልገዋል።”*

*“አዲስ የቢሮ ሕንፃ በሚኖርበት ሰዓት፣ ከሚዘንበው የጣራ ዝናብ ውስጥ አንዳንዱን ማቆር እንዲቻል አረንጓዴ ጣራ እንዲኖር ሕግ ማውጣት።”*

*“በተለይ ከከፋ ሙቀት እና ቅዝቃዜ፣ ከአየርንብረት ድንገተኛ ጉዳት ጥበቃ ሲደረግባቸው የሚገቡት የጎዳና ተዳዳሪ ሰዎችን በተመለከተ እጨነቃለሁ። የከፋ ሙቀት ሲመጣ ጊዜ ውሃ ያስፈልጋቸዋል።”*

*“ውሃችን ልክ እንደ መኪና ማቆሚያ ወይም ኮንክሪት የመሳሰሉ መሬቶች ላይ ሳይሆን ወደ አፈር ውስጥ መዝነቡ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት መሬቶች ላይ ውሃ መውረድ አንዴ ካቆመ በኋላ፣ የሚከሰተው በመተላለፍያ መንገዱ ወይም ኮንክሪቱ ላይ ያለውን ልክ እንደ ነዳጅ ዓይነት ብክለትን በመሰብሰብ እና በቀጥታ ወደ ባህር ዳርቻው ይገባል።”*

“አንዳንድ አስፋልት መንገዶች፣ በተለይ በአውሎንፋስ፣ ጥልቅ አዘቅት ወቅት፣ ደራሽ ጎርፍ ይኖራቸዋል። ለደራሽ ጎርፍ የበለጠ ተጋላጭ የሆኑ አንዳንድ ቦታዎች ያሉ እንደሆነ፣ ካውንቲው ሰዎችን ማስጠንቀቅ ወይም በጣም ዋነኛ አውሎንፋሶች በሚከሰቱበት ሰዓት ከእነዚህ ቦታዎች ለቀው እንዲሄዱ ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈልገዋል።

“ከማህበረሰቤ ጋር በጋራ አብሬ ለማደግ የማህበረሰብ ጓሮ አትክልት ማየት እፈልጋለሁ።”

## በማህበረሰብ ዉይይት የተነሱ ዋና ፍሬ ነገሮች

# የመካች አምባሳደር የዳሰሳ ጥናት

“ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ግብዓቶች እንዲኖሩ ማየት እፈልጋለሁኝ።”

“ ለሕዝቡ የአየር ንብረት ለውጥ ግብዓቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ፣ ብዙሃነትን የሚያከብሩ የአየርንብረት ፍትህ/የዘር ፍትህ ዝግጅቶችን ማዘጋጀት እና የአየርንብረት ለውጥ በእነሱ ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ በተመለከተ ማህበረሰቡን ማስተማር አለበት።”

“ እንግሊዘኛ ለመናገር የማይችሉ ከሆነ ለሁሉም የማህበረሰቡ አካላቶች ድምፃቸውን ማሰማት አደጋች ይሆንባቸዋል። በብዙ ቋንቋ የተዘጋጁ የዳሰሳ ጣቶች ያስፈልጉናል።”

“ የሚያስፈልገውን ለውጥ እንድንገፋበት እኛን ማየት እፈልጋለሁኝ።”

“ በስርዓት የተደገፈ የዘር መድሎን ከግምት ውስጥ ለማስገባት የታሪክ ትምህርት የሚሰጥበትን መንገድ መቀየር አለብን።”

“ በተለይ በችግር ጊዜ ወቅት፣ የእኔ ማህበረሰብ እርስበእርስ ራሱን እንደሚጠብቅ እና ለእያንዳንዱ ሰው በጋራ በመቆሙ በማወቄ በጣም ደስተኛ ያደርገኛል።”

“ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ለቤተሰቤ አስተማማኝ፣ የሥነ-ምህዳር ጥበቃ ያለበት ቦታ እንዲሆን እፈልጋለሁኝ።

“ እኛ ተማሪዎች አወንታዊ ለውጥ ለማምጣት እየፈጠርን ያለውን ነገር ማየት በጣም አስደሳች ነው።”

“ የጥቁር ዘር ያለባቸው ማህበረሰቦች የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በጋራ ለመፍታት ብዙ ጥረቶች እንዲደረጉ ማየት እፈልጋለሁኝ። ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸው ሰዎች ልክ እንደ እያንዳንዱ ሰው [ተመሳሳይ] ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት እንዲችሉ እፈልጋለሁኝ።”